# ሐሺም መስጂድ

## በቀደምት ሀገራዊ ዑለማዕ ሥም የተሰየመ መስጂድ

**የተመሰረተበት ዘመን:-** ከ1945-1949 ዓመቱ ላይ የመረጃ ምንጮቻችን ተለያይተዋል:: አንዳቸው በ1945/6 አካባቢ ነው ሲሉ ሌላኛው ደግሞ በ1949 ነው ብለዋል:: በመሆኑም ጊዜው ከ1945-1949 ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑ እሙን ስለሆነ አስቀምጠነዋል::

**የሚገኝበት አካባቢ:-** ከአውቶቡስ ተራ ከፍ ብሎ፣ ገነሜ ት/ቤት አካባቢ፣ አባድር ት/ቤት አጠገብ

**የሥሙ ትርጉም:-** አው ሐሺም ተብለው የሚታወቁ ታላቅ ዓሊም በሀረር የነበሩ ሲሆን መስጂዱ ለሳቸው መታሰቢያ ሆኖ የተሰየመ ነው ሲሉ ሐጂ አህመድ ዩሱፍ ኸለፍ አጫውተውናል:: እንዲህ በቀደምት ሀገራዊ ዑለማዕ ሥም የሚሰየሙ መስጂዶች እንዲበዙ እንመኛለን::

**መግቢያ:-**

በ20/03/2002 በአስር ሰላት ሀሺም መስጂድ ሄድኩ:: የሄድኩትም ስለ መስጂዱ ታሪክ ያቀረብነው ጥያቄ ለረዥም ወራት ሳይመለስ በመቅረቱ ነበር:: ሠላት ላይ ደርሼ ተቀላቀልኩ:: ባይኔ ሳማትር የማውቀው ሰው አላገኘሁም:: ብቻ ከኢማሙ ጋር በአይን ተገናኘን:: ኢማሙ አሰግደው ካበቁ በኋላ ፊታቸውን ወደ ጀመዓቸው አድርገው በጣታቸው ተዝኪራ ሲያደርጉ ተመለከቱኝ:: እኔም ከረባትና ኮት ለብሰው ስላየኋቸው «እኚህ ኢማም ቀልጣፋ ሳይሆኑ አይቀርም:: ጉዳዩን ለርሳቸው አቅርቤ መላ በሉኝ ልበል» እያልኩ በማሰብ እያየኋቸው ስለነበር በአይን ተጋጨን:: መላልሰው ተመለከቱኝ:: እኔም አይኔን ከርሳቸው አልነቀልኩም ነበር:: በእለተ እሁድ ወጣቶች በስንት ነገር ሲዝናኑ እኔ በመስጂዶች ታሪክ ተጠምጄአለሁኝና እዛ ሄጄ ያለ ውጤት ላለመመለስ ቆርጫለሁኝ:: እርሳቸውም አስተያየቴ የምር መሆኑ ገብቷቸዋል:: ዱዓ አድርገው እንደጨረሱ «አሰላም አለይኩም ያ ኡስታዝ» ብዬ ሠላምታ ሰጠሁ:: በጥሩ ፈገግታ ተቀበሉኝ:: ራሴንና ስለመጣሁበት ጉዳይ አስተዋወኳቸው:: ወዲያውኑ ተረዱኝ:: «ከዚህ ቀደም የላካችሁት መጠይቅ ደርሶን ነበር:: ነገር ግን እንደዚህ በአካል ስላልመጣችሁ አልሞላነውም» አሉኝ:: እኛ ደግሞ እነርሱ ሞልተው እንዲልኩልን እየጠበቅን ነበር:: ለማንኛውም አሁን ተገናኝተናልና ባጭር ቀጠሮ ተገናኝተን ብናጠናቅረው





ተባብለን ለ21/03/2002፣ መግሪብ ሰዓት ተቀጣጠርን:: ኮሚቴዎችና የመስጂዱ ታሪክ አዋቂዎችን ይዘው ሊጠብቁኝ ተነጋግረን ተለያየን:: ያለ ምንም ውጣ ውረድ ነገሩን ስላቀለሉልኝ በጣም ተደሰትኩ:: አመሰገንኳቸው::

ለካ ሳላውቀው ለጉዳዩ (ለመስጂዱ) ዋና ከሆኑ አንዱ ሰው ጋር ተገናኝቼ ኖርዋል!? ሐጂ ኑሩ መሐመድ ይባላሉ:: የመስጂድ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ ናቸው:: ዋናው ኢማሙ ለአረፋ ወደ ሀገር ቤት ስለሄዱ እስኪመለሱ ምትክ ሆነው በማሰገድ ላይ ሆነው ነው ያገኘኋቸው::

ሐጂ ኑሩ መሐመድ ቃላቸውን አላጠፉም፣ ቀጠሯችንን አላፈረሱም:: እንደተ ባባልነው በ21/03/2002 መግሪብ ሰዓት ተገናኘን:: ሌሎች ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎችም ነበሩ:: እያዳንዳቸው የተለያየ ተሰጥኦ ያላቸው፣ ኢማናቸው ከፊታቸው የሚነበብ፣ አስደሳችና ተግባቢ የሆኑ አባቶች ሆነው ነው ያገኘ ኋቸው:: መሰሉ ነገር በሌላ ቦታ ብዙም አላጋጠመኝ:: በጣም ተደሰትኩ:: ረካሁ:: ለካ ለአላህ መሰሉ ሰውም አለው? ማለቴ አልቀረም::

**አመሰራረት:-** መስጂዱ የተመሰረተው ሐጂ አብዱላሂ ኻሊድ በተባሉ የሀ ረሪ ተወላጅ አማካኝነት ነው:: ሐጂ አብዱላሂ ከሀረር በመምጣት በአዲስ አበባ የንግድ ሥራ ድርጅት ካቋቋሙ ሰዎች አንዱ ናቸው:: በተለይም በሀሺም መስጂድ ጎረቤት የሚገኘው የሰለሃዲን መስጂድ መስራች ከሆኑት ሐጂ ዩኑስ አህመድና ከሌሎችም ጋር በመሆን አንድ ታዋቂ የልብስ ስፌት ድርጅት እንደነበራቸው ይገለፃል:: ይህም ድርጅት ከፒያሣ አወሊያ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፊት ለፊት፣ ከማስሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኢንስቲቱሽን (የድሮ ማስታወቂያ ሚኒስቴር) አጠገብ እንደነበር ይነገራል:: ድርጅቱ የሀገሪቱ የፖሊስ፣ የጦርና የክብር ዘበኛ ሚሊታሪ ዩኒፎርሞችን በጨረታ በማሸነፍ ይሰራ እንደነበር ተራኪዎቻችን ያስታውሳሉ:: የዚህ ታዋቂ ድርጅት መስራቾች ተራኪዎቻችን በሚያስታውሱት ያህል:-

1. ሐጂ ዩኑስ አህመድ (የሰለሃዲን መስጂድ መስራች)
2. ሐጂ አብዱላሂ ኻሊድ (የሀሺም መስጂድ መስራች)
3. ሐጂ አብዱልሃፊዝ በርኸድሌ
4. ሐጂ ዱሪ አብዲቦር
5. ሐጂ ሙሐመድ ሸሪፍ
6. ሐጂ አብዱላሂ አዱስ. . . ይገኙበታል::

ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ:: የዚህ መረጃ ምንጮች ለጊዜው ያስታወሷቸው እነዚህ

ናቸው። ይህም የሚያስረዳን የቀድሞ አባቶቻችን በኢማን ብቻ ሳይሆን በቢዝነስ ፈጠራና አመራርም አሁን ካለው ትውልድ ብዙ ይበልጡን እንደነበር ያመላክታል። ምክንያቱም በዛን የጥንት ጊዜ የሼር ድርጅትን በማቋቋም እንዴት ትልቅና ዘመናዊ ሥራ መስራት እንደሚችሉ ተረድተው የተገበሩት ሆነው እናገኛቸዋለን። በአሁኑ ጊዜ በተለይ የጋራ ሥራ ድርጅት ምን ያህል አስፈላጊና አዋጭ እንደሆነና የግል የተናጠል ሥራ ምንም ያህል ገንዘብ ቢኖር የትም ሊያደርስ እንደማይችል መረዳት ሳይችሉ በመቅረት ትልቅ ቢዝነስ መፍጠር ሳይችሉ የቀሩ አያሌ ሙስሊሞች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ አባቶቻችን የቢዝነስ ፈጠራና አመራር ባህል ሊማሩ ይገባል እንላለን።

ወደ መስጂዱ ታሪክ ስንመለስ ሐጂ አብዱላሂ ኻሊድ ከላይ ከተገለጹት ወንድሞቻቸው ጋር የጋራ ታዋቂ የሥራ ድርጅት በመመሥረት እየሰሩ እያለ አሁን መስጂዱ ያለበት ቦታ ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር ቦታ ገዝተው መኖር ይጀምራሉ። በጊዜው አካባቢው ወጣ ያለ፣ ዳር የሚባልና ጫካ የነበረ እንደነበር ይነገራል። በዚህም ቦታ በጋራ መሬት በመግዛት ብዙ የሀረሪ ተወላጆች ይሰፍራሉ። ሐጂ አብዱላሂም አሁን መስጂዱ ያለበትን ይዞ ከመስጂዱ ተያይዞ በስተደቡብና ምዕራብ ያለውን ቦታና መሬት ይመሰርታሉ። ቤታቸውን ገንብተው መኖር በጀመሩ በጥቂት ወራት ያህል ጊዜ ውስጥ መስጂዱን እንደገነቡ ይነገራል። እርሳቸው በመጀመሪያ ያስገነቡት መስጂድ አሁንም ግርግዳው ያለ ሲሆን 9 X በ7 የሆነ ነበር። ይህም የመስጂዱ ሰሜናዊ አቅጣጫ ማለትም የኢማሙ ሜንበርን ይዞ በስተግራ ጥግ ያለው የመስጂዱ ግርግዳ በርሳቸው ጊዜ የተሰራና አሁንም እንዳለ ያለ ነው። የተሰራውም በግንብ ነው። በሂደት መስጂዱ ወደ ኋላና በቀኝ በኩል ጎን መስፋፋት የተደረገለት ቢሆንም በግራ በኩል ያለው የፊት ለፊት አካሉ ግን ምንም አልተነካም።

በጊዜው መስጂዱ ሲገነባ በዙሪያው የሚገኙ ቤተሰቦች ከ10 የማይበልጡ እንደነበር በማስታወስ ለጀመዓ ሶላት ይገኙ የነበሩት የመስጂዱ መስራችና ባለቤታቸው ሐጂየት ፋጡማ አብደላህ፣ ሐጂ አብዱልሃፊዝና ባለቤታቸው፣ ሐጂ ዩኑስ ኸለፍ፣ ሐጂ ኑሩ መሐመድ፣ ሐጂ አብዱልሃሚድ ዘይድ፣ ሐጂ መሐመድ ከማል.. . . ይገኙበት ነበር። ከነዚህም ውስጥ ሁለቱ አሁን የዚህ መረጃ ምንጭ ለመሆን በቅተዋል (ሐጂ ኑሩ መሐመድና ሐጂ መሐመድ





ከማል)። የመስጂዱ መስራች ሐጂ አብዱላሂ ኻሊድ መስጂዱን ሲመሩና የሚያስፈልገውን ሁሉ እየሸፈኑ እስከ 1970ዎቹ ቆይተዋል። በኋላም እድሜቸው እየገፋ በመሄዱ በ1970ዎቹ ለኮሚቴዎች አስረክበው እርሳቸው እንደ ማንኛውም ጀመዓ ሰጋጅ ሆነዋል። በ1998 ላይም በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። (አላህ የጀነት ሰው ይበላቸው-አሚን)

<u>መስጂዱ አሁን ያለበት ደረጃ:-</u> መስጂዱ መጀመሪያውኑ የተገነባው በድንጋይ ግንብ በመሆኑ የቀድሞ ከፊል ገጽታው እንዳለ እንዲቀጥል አድርጎታል። በኋላ የተስፋፋው አካሉም በመሰሉ ግንብ የተሰራ ስለሆነም መስጂዱ ሙሉ በሙሉ በግንብ የተገነባ ነው። መስጂዱ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ይዞታ በሙሉ ለመስገጃነት የተጠቀመበት ሲሆን 16 X በ8 አካባቢ የሆነ ነው።

<u>የይዞታ ስፋት:-</u> አጠቃላይ የይዞታ ስፋቱ ከውስጥ በኩል 16 X በ11 አካበቢ የሆነ ነው። የሚሰገድበት ቦታ 16 X በ8 በሆነው አካባቢ ነው። 16 X በ3 የሚሆን ቦታ ለውዱዕ ቦታ ለአንዳንድ እቃዎች ማስቀመጫ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል። የጫማ ማስቀመጫም ከበሩ በኩል የተወሰነ ቦታ ይዟል። በመሆኑም በአጠቃላይ 16 X በ11 ሆኖ 176 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

<u>ሚናራ:-</u> በግምት ወደ 5 ሜትር ከፍታ ያለው ሚናራ ያለው ነው።

<u>መስፋፋቶች:-</u> መስጂዱ በመጀመሪያ ሲገነባ 9 X በ7 በሆነ ስፋት እንደሆነ ተመልክተናል። በኋላም በደርግ ዘመነ መንግስት ሁለት ጊዜ መሻሻሎችን በማሳየት አሁን ወዳለበት ደረጃ ደርሷል። የመጀመሪያው መሻሻል 9 X በ3 አካባቢ የሆነ ስፋት ከኋላ በኩል የተሳበለት መሆኑ ነው። ቀጥሎም 7 X በ11 የሆነ በቀኝ በኩል ተጨመረለት። በአጠቃላይ 9 X በ7 የመጀመሪያው (63 ካ.ሜ)፣ 9 X በ3 (ከኋላ በኩል የተሳበው 27 ካ.ሜ)፣ 7 X በ11 (በቀኝ ጎን በኩል የተጨመረው 77 ካ.ሜ) በድምሩ 167 ካ.ሜ ሆነ ማለት ነው።

<u>የሰጋጁ ብዛት:-</u> መስጂዱ በሁሉም የሠላት ወቅት የሚሞላ ነው። በተለይም ደግሞ የመግሪብና የኢሻ ሰላት ወቅት መስጂዱ ጠቦ በተራ እንደሚሰገድ ተገልፆዋል። ይህም ማለት አንደኛው ዙር ሰግዶ ሲጨርስ ቦታውን በመልቀቅ ሌላው ዙር ይከተላል ማለት ነው። ይህም በመሆኑ መስጂዱ አያሌ ሰጋጆች ያሉት ነው። መስጂዱ በአንድ ጊዜ በውስጡ ሊይዝ የሚችለው ሰው በተለመደው

ስሌታችን በአንድ ካ.ሜ ቦታ ሁለት ሰው ሂሣብ 167 ካ.ሜ X በ2 ሰዎች=334 ሰዎችን የማስተናገድ አቅም አለው ማለት ነው።

<u>**የሴቶች መስገጃ ቦታ፡-**</u> መስጂዱ የሴቶች መስገጃ ቦታ የለውም። ይህም የሆነው ያለው ቦታ ጠባብ በመሆኑና የሠጋጁ ብዛት ከፍተኛ ስለሆነ ነው። ለወደፊቱ ግን መስጂዱ በፎቅ መሰራት ከቻለ ችግሩን ማስወገድ ይችል ይሆናል።

<u>**ኢማሞች፡-**</u>

1. ሐጂ አብዱላሂ ሸሪፍ (የመጀመሪያው ኢማም ነበሩ)
2. ሐጂ ጃሚ አቦች
3. ሸኽ ዳውድ (ወሎዬ)
4. ሸኽ መሐመድ ኑር ወሎዬ (ለብዙ ዓመታት እንዳገለገሉ ይገለፃል)
5. ሸኽ ጂብሪል አብዱላሂ (ወደ 30 ዓመታት ማገልገላቸው ይነገራል)
6. ሸኽ ሳቢት ዳሪ (ከ1999-አሁን)

ምክትል ኢማም ብዙን ጊዜ የሌለ ሲሆን በሸኽ ጂብሪል አብዱላሂ ጊዜ ብቻ ሸኽ መሐመድ አብዱልቃድር የተባሉ ም/ኢማም እንደነበሩ ይታወቃል።

<u>**ሙአዚኖች፡-**</u>

1. በመጀመሪያ አካባቢ የአካባቢው ሰጋጅና ቤተሰቡ እንደተገኘ ያገለግል ነበር።
2. ሸኽ ከቢር ሙሐመድ ሸኽ የተባሉ ሰው በመሀል አካባቢ በዚህ አገልግሎት ሰጭነት ይጠቀሳሉ። እኚህ ሰው የ70ዎቹ ዓመታት ሸማግሌ ሆነው እስፖርት የሚወዱና የሚሰሩ፣ ጅምላስቲክ በመስራት እንደፈለጉ እጥፍ ዘርጋ የሚሉ፣ በጊዜው ማይክራፎን ስላልነበር ሚናራው ላይ ወጥተው አዛን የሚሉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

<u>**የኢልም ፕሮግራሞች፡-**</u>

1. ሐጂ ዑመር ውዳቶ (በ1970ዎቹ አካባቢ በመስጂዱ ውስጥ ለትላልቅ ሰዎች የቁርአን ቂርአት ትምህርት ይሰጡ ነበር)።
2. ሐጂ አህመድ ዓሊ መላቅ (የፊቂህ ትምህርት ያስተምሩ ነበር)
3. ሸኽ ሀሚድ ዩሱፍ (የፊቂህ ትምህርት ይሰጡ ነበር)
4. ሸኽ ሰኢድ አህመድ ሙስጠፋ (በ1980ዎቹ የተፍሲርና የሲራ ፕሮግራሞች ነበሯቸው። እኔ (ፀሃፊው) የርሳቸውን ፕሮግራም በጊዜው እከታተለው የነበረ ሲሆን በአማካኝ ወደ 200 የሚጠጉ ሰዎች የሚከታተሉትና ተወዳጅ እንደነበር አስታውሳለሁ)።





5. ሸኽ መሐመድ አህመድ አል-ባሲጥ (አሁንም ድረስ ዘወትር ማክሰኞ ቀን፣ ከመግሪብ እስከ ኢሻ፣ የተፍሲር ፕሮግራም ያካሄዳሉ)
6. ሸኽ ዩሱፍ ሸሪፍ (ዘወትር እሮብ፣ ከመግሪብ እስከ ኢሻ፣ ተጅዊድ ያስተምራሉ)
7. ሸኽ ቃሲም ሐጂ (ከማክሰኞችና ከእሮብ ውጪ ባሉት ቀናት ዘወትር፣ ከመግሪብ እስከ ኢሻ፣ ተፍሲር፣ ሲራና ፊቂህ በማስተማር አገልግሎት ይሰጣሉ)።

<u>**የመስጂዱ ኮሚቴዎች**</u>

1. ሐጂ አህመድ ዩሱፍ. . . . . . . . . . . . . . . . . .ሰብሳቢ
2. ሐጂ ኑሩ መሐመድ መረራ. . . . . . . . . . . . .ም/ሰብሳቢ
3. ሐጂ መሐመድ ከማል ኢስማኢል. . . . . . . . . .አባል ናቸው።

<u>**ጥቂት ስለ መረጃ ምንጮቼ፡-**</u>

የመስጂዱ አመራር ኮሚቴ ሆነው በማገልገል ላይ ያሉት የመረጃ ምንጮቻችን መስጂዱ ከተመሰረተበት ዘመን ጀምረው የነበሩና አሁንም ያሉ አንጋፋ ሰዎች ናቸው። አንጋፋ ሰዎች ከመሆናቸውም በተጨማሪ በዚህ እድሜአቸው (80፣78፣75 ዓመታት በቅደም ተከተላቸው) ሆነውም አሁንም ጠንካራ፣ አስታዋሽ፣ ተግባቢ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። እንደ እድሜአቸው ሳይሆን በብዙ ነገር ከወጣቶች ሁሉ የሚሻሉ ሆነው ነው ያገኟቸው። ቅንነት፣ ትብብር፣ ተግባቢነት፣ ፈገግታ. . .ያለው ባህሪያቸው ደግሞ የኢማናቸው ደረጃን የሚገልጽ ነው። ብርቱ፣ ጠንካራና የድሮውን ሳይረሱ ያለ አንዳች የጽሑፍ ማስታወሻ አንድ በአንድ የሚያስረዱ የመሆናቸው ተሰጥኦ አስገርሞኛል። ለዚህም ነው ከርዕሱ ቀጥሎ ያለው ርዕስ ወጣት በሚመስሉ አባቶች የሚመራው መስጂድ የተባለው። አላህ ይጨምርላቸው፣ አላህ እድሜአቸውን ያርዝመው. . .እያልኩኝ ላደረጉልኝ ፈጣንና መልካም ትብብር ከልብ አመሰግናለሁኝ።

<u>**የመረጃ ምንጮች፡-**</u>

1. ከላይ የተጠቀሱት የመስጂዱ አመራሮች
2. ዑስታዝ መሐመድ አሚን (የመድረሳው ኃላፊ) ናቸው።

<u>**የስልክ አድራሻ፡-**</u>

**011-2-13 68 46፣ 0913-73 21 92**